

# ህግ ከማስከበር በዘለለ

## በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በኢትዮጵያ የፀጥታ ሀይሎች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

AMNESTY INTERNATIONAL

አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ የአለም ሕዝቦች ሁሉ ሰብዓዊ መብታቸው እንዲከበርላቸው የሚታገሉ ከ7 ሚሊዮን በላይ አባላት ያሉት አለምዓቀፋዊ እንቅስቃሴ ነው።

ራዕያችን የሰው ልጆች ሁሉ፣ በዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ እና በሌሎች የዓለማቀፍ ሰብዓዊ መብት መስፈርቶች የተቀመጡት መብቶች ተከብሮላቸው ማየት ነው።

ከማንኛውም መንግስት፣ ፖለቲካዊ ርዕዮተአለም፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይም ሀይማኖት ነፃ ነን፤ የገንዘብ ምንጫችንም በዋናነት ከአባላቶቻችን እና ከህዝብ የምናገኘው ልግሳ ነው።

© Amnesty International 2020
Except where otherwise noted, content in this document is licensed under a Creative Commons (attribution, non-commercial, no derivatives, international 4.0) licence.
https://creativecommons.org/licenses/by-nc-nd/4.0/legalcode
For more information please visit the permissions page on our website: www.amnesty.org
Where material is attributed to a copyright owner other than Amnesty International this material is not subject to the Creative Commons licence.
First published in 2020
by Amnesty International Ltd
Peter Benenson House, 1 Easton Street
London WC1X 0DW, UK

**Index: AFR 25/2358/2020**
**Original language: English**

**amnesty.org**

***Cover photo:*** *© Amnesty International (Illustration: Victor Ndula)*

# ማውጫ


1. ዋና ዋና የማጠቃለያ ሀሳቦች 4

2. ማጠቃለያ እና ምክረ-ሀሳቦች 6

2.1 ማጠቃለያ 6

2.2 ምክረ- ሀሳቦች 6

2.2.1 ለኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር 7

2.2.2 ለመከላከያ ሚኒስቴር 7

2.2.3 ለሰላም ሚኒስቴር፣ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና ለጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ 7

2.2.4 ለሰላም ሚኒስቴር 7

2.2.5 ለተባበሩት መንግስታት፣ ለአፍሪካ ሕብረት እና ለኢጋድ 8

2.2.6 ለአውሮፓ ሕብረት፣ ለአሜሪካ መንግስት፣ ለታላቋ ብሪታኒያ፣ ለካናዳ፣ ለቻይና፣ ለኬንያ፣ ለደቡብ አፍሪካ 8

# 1. ዋና ዋና የማጠቃለያ ሀሳቦች

አሁን በስልጣን ላይ ባለው መንግስት በ2010 ዓ.ም የተጀመረው ፖለቲካዊ ለውጥ ሀገሪቱን ተጠናውተዋት ከነበሩት አስከፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ ከፍርድ ውጭ ሰው ከመግደል፣ ሰዎችን ከማሰቃየትና መሰል ሌሎች ኢሰብዓዊ አያያዞች፣ ሰዎችን ያለፈቃዳቸው እንዲሰወሩ ከማድረግ እና ከመሳሰሉ የመብት ጥስቶች እንድትላቀቅ አጋጣሚውን ፈጥሮላታል።

ከተደረጉት ለውጦች ውስጥ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች መለቀቅ፣ በስደት ላይ የነበሩ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ በመፍቀድ የፖለቲካ ፓርቲዎቻቸውን በህጋዊ መንገድ እንዲያስመዘግቡ ማድረግ ፣ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የሀገር ውስጥ ዜና ማሰራጫዎችን፣ የሲቪክ ማህበራትን እና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለማሽመድመድ መንግስት ይጠቀምባቸው የነበሩትን እንደ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እና የፀረ ሽብር አዋጆች ያሉ ህግጋትን መሻር ተጠቃሽ ናቸው።

የሰብዓዊ መብት ሁኔታዎችን ለማሻሻል የተወሰዱ የመጀመርያ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በፀጥታ ሀይላት ያለማሳለስ እየተወሰዱ ያሉ ኋላቀር የሀይል እርምጃዎች በዘላቂነት ሊቀጥል የሚገባውን ለውጥ ባጭር እንዳያስቀሩት ያሰጋል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል በ2011/12 ዓ.ም በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች በተከሰቱ ማህበራዊ ግጭቶች ዙሪያ ጥናት አካሂዶ ነበር። ጥናቱ እንደሚያሳየው፣ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይሎች፣ የየክልሎች ልዩ ፖሊስ ሀይል እና የአካባቢው አስተዳደር አካላት፣ ከታጠቁ የሚሊሻ ወጣቶች ጋር በመሆን ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በተወሰኑ የኦሮሞና የአማራ ክልሎች ላይ ፈጽመዋል። እነዚህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ በኦሮምያ ክልላዊ መንግስት፣ በምዕራብ ጉጂና በምስራቅ ጉጂ ዞኖች የተከሰቱ ሲሆን፣ በአማራ ክልላዊ መንግስት ደግሞ፣ በምዕራብ ጎንደርና በማዕከላዊ ጎንደር ዞኖች ተመሳሳይ ድርጊቶች ተፈጽመዋል።

የአምነስቲ ኢንተርናሽናል አጥኚዎች እንዳመለከቱት፣ በኦሮሚያ ውስጥ በሁለቱ የጉጂ ዞኖች የተሰማሩ የፀጥታ ሀይላት፣ ህገወጥ ግድያዎችን፣ በዘፈቀደ የሚደረጉ እስራቶችን፣ ማሰቃየትን፣ ሌሎች ኢሰብዓዊ አያያዞችን፣ አስገዳጅ ማፈናቀሎችን እና ሀብት ንብረትን የማውደም ግፍ ፈጽመዋል። በአማራ ክልል ደግሞ፣ የክልሉ ልዩ የፖሊስ ሀይል አካላት ከየአካባቢው የአስተዳደርና ሚሊሻ ጋር በማበር በምዕራብና ማዕከላዊ ጎንደር ውስጥ በሚኖሩ የአማራና የቅማንት ህብረተሰብ መካከል የርስ በርስ ግጭት እንዲነሳ እንዳደረጉ አጥኚዎቹ በቂ መረጃ አግኝተዋል።

**የትጥቅ ጥቃት**

የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ መንግስት፣ የሰብዓዊ መብትን ለማሻሻል የወሰደውን እርምጃ ተከትሎ፣ ወታደራዊ ተቃውሞንና የርስ በርስ ማህበራዊ ግጭቶችን ያስከተሉ ፖለቲካዊና ብሄር ተኮር ውጥረቶች በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሀረር፣ በድሬዳዋ፣ በቤኒሻንጉል እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ውስጥ ታይተዋል። እራሱን የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት (ኦ.ነ.ሠ) እያለ የሚጠራው ታጣቂ ቡድን በምእራባዊና ደቡባዊ ኦሮሚያ ክልል የትጥቅ ጥቃት አድርሷል። ኦ.ነ.ሠ፣ ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦ.ነ.ግ) ወታደራዊ ክንፍ የተገነጠለ አካል ነው፤ ኦ.ነ.ግ በሰላማዊ መንገድ ፖለቲካዊ አጀንዳውን ለማስፈጸም፣ በመስከረም 2011 አገር ውስጥ ከመግባቱ አስቀድሞ፣ ከሀገር ውጭ ወታደራዊ ትግል ሲያደርግ የነበረ ድርጅት ነው።

ለኦ.ነ.ሠ የትጥቅ ጥቃት አጸፋዊ ምላሽ፣ መንግስት የኮማንድ ፖስት በማቋቋም፣ ጥር 2011 ዓ.ም ህግ የማስከበር ጥቃት አካሂዷል፤ ኮማንድ ፖስቱ፣ በክልላዊና በፌዴራል መንግስት ጥምረት የሚካሄድ የተቀናጁ የዘመቻ ስራዎችን አስተባብሯል። ከዚህም በተጨማሪ፣ መንግስት፣ በአማራ፣ በሀረርና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች የተከሰቱ የርስ በርስ ማህበራዊ ግጭቶችን ለመቆጣጠር ኮማንድ ፖስቶችን ተጠቅሟል።

የአምነስቲ ኢንተርናሽናል አጥኚዎች፣ በዋና ከተማው አዲስ አበባ እና በጎንደር ደግሞ፣ በአይከል፣ በአይምባ እና በወልቃ እንዲሁም በሀዋሳ ከ80 በላይ የሚሆኑ ግለሰቦችን አነጋግረዋል። ከእነዚህ መካከል በዋናነት የጥቃት ሰለባዎችና የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሲፈጸም ያዩ የዓይን እማኞች ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ ሃያዎቹ ሴቶች ነበሩ። የዓይን እማኞቹ፣ አርሶ አደሮችን/አርብቶ አደሮችን፣ የንግድ ማህበረሰቡ አባላትን፣ ተማሪዎችን፣ የመንግስት ሰራተኞችን፣ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን እና መምህራንን ያካተተ ነበር። የአምነስቲ ኢንተርናሽናል አጥኚዎች በጎንደር ከተማ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሀላፊንና በማዕከላዊ ጎንደር የሰላምና የፀጥታ ክፍል ሀላፊን ጭምር አነጋግረዋል። የተለያዩ ሰነዶችን፣ የዜና ዘገባዎችን፣ የተጎጂ ፎቶግራፎችና የሳተላይት ምስሎችንም መርምረዋል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል ስላካሄደው ጥናት ምላሽ እንዲሰጡት፣ የሰላም ሚኒስቴርን፣ የመከላከያ ሚኒስቴርን፣ የፌዴራል አቃቢ ህግን፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንን፣ የኦሮሚያ ክልል የፀጥታና የአስተዳደር ጉዳዮች ቢሮን፣ የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽንን፣ የአማራ የፀጥታ ቢሮን እና የአማራ ፖሊስ ኮሚሽንን ጠይቋል። ይሁን እንጂ፣በተለያዩ የጥናቱ ደረጃዎች ስለጥናቱ ግኝቶች በኢሜል፣ በስልክ ወይም በአካል አስተያየት እንዲሰጡ የተጠየቁት እነዚህ አካላት፣ ከአማራ ክልል የፀጥታ ቢሮ በስተቀር ምላሽ ሳይሰጡ ቀርተዋል። ለአማራ ክልል የፀጥታ ቢሮ ምላሽ በመስጠቱ ምስጋና እናቀርባለን።

**ያለፍርድ የሚፈጸም የሞት ቅጣት**

የጥናታችን ውጤት እንዳረጋገጠው፣ ከጥር 2011 ዓ.ም አንስቶ፣ በኦሮሚያ ክልል፣ ምስራቅ ጉጂ ዞን ውስጥ በሚገኘው ጎሮ ዶላ ወረዳ እና ምእራብ ጉጂ ውስጥ በሚገኘው ዱግዳ ዳዋ ወረዳ፣ ቢያንስ 39 ሰዎች ያለ ፍርድ ተገድለዋል። ከእነዚህ ያለ ፍርድ ከተገደሉ ሰዎች መካከል፣ አራቱ (አብዱላሂ ጎሉ ሀላልቄ፣ ቦዲሻ ጨልቄ፣ ቃንቄ ኡቱራ እና ደደቻ ሚኤ'ሳ ሀላልቄ) ዘመዳሞች ነበሩ። የቤተሰብ አባላቶቻቸውም በተደጋጋሚ በዘፈቀደ ሲታሰሩ ቆይተዋል። አብዱላሂ፣ ደደቻ እና ኡቱራም ሞተው የተገኙት፣ የኢትዮጲያ የመከላከያ ሀይል (ኢ.መ. ሀ) ወታደሮች ከእስር በለቀቋቸው ማግስት ጠዋት ላይ ነበር።

**የዘፈቀደ እስር**

በሁለቱ የጉጂ ዞኖች ውስጥ ተሰማርቶ የነበረው ኮማንድ ፖስት፣ የኦ.ነ.ሠ እና የኦ.ነ.ግ ደጋፊዎች ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ ሰዎችን በዘፈቀደ አስሯል። አንዳንዶቹ፣ ለተደጋጋሚ እስራት ሲዳረጉ፣ በሺዎች የሚቆጠሩት ደግሞ በምእራብና ምስራቅ ጉጂ ውስጥ በሚገኙ የአካባቢው ፖሊስ ጣቢያዎች ረዘም ላሉ ጊዚያት በእስር ቆይተዋል። ኮማንድ ፖስቱ፣ ከተለያዩ የኦሮሚያ ክፍሎቻ ያሰባሰባቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ ታሳሪዎች ወደ ጦላይ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ አግዟል፤ በዚያም፣ በህግ የበላይነት፣ በህገ-መንግስታዊ ስርዓት እና በኦሮሞ የትግል ታሪክ ዙሪያ የግዴታ ሥልጠናዎችን እንዲወስዱ ተደርጓል። በተጨማሪም፣ በቡድን ውይይት ወቅት፣ ጥፋተኛ ነን ብለው እንዲያምኑ ተደርገዋል። ምንም ጥፋት የለብንም ያሉት ደግሞ፣ ወደ ሳንቃሌ ኦሮሚያ ፖሊስ ኮሌጅ እንዲዛወሩ ተደርጎ፣ ቢያንስ 2,000 የሚሆኑት ለወራት በእስር እንዲቆዩ ተደርጓል። በተለይ በሳንቃሌ የነበረው የእስር ሁኔታ አሰቃቂ ነበር። ይህም የሆነው ፣ በምግብና መኝታ እጥረት እንዲሁም በማሰቃየትና በሌሎች ኢሰብዓዊ አያያዞች የተነሳ ነበር። ጠዋትና ማታ ከምትፈቀድ የ10 ደቂቃ እረፍት በስተቀር፣ እስረኞች ቀኑን ሙሉ ተቆልፎባቸው ይውሉ ነበር ።

**አስገድዶ ማፈናቀል**

በገጠሩ የጎሮ ዶላ ወረዳ አካባቢ የሚኖሩ ከፊል አርብቶ አደር አባላት ከሚኖሩበት ቀዬ ተገደው ይፈናቀሉ ነበር። ይህም ኮማንድ ፖስቱ ህግን ለማስከበር የሚጠቅምበት ስትራቴጂ አካል ነበር። ይህ ከፊል አርብቶ አደር የሆኑትን የማህብረሰብ አባላት በግድ ከየቀያቸው እያፈናቀሉ ወደ ሌላ ቦታ የማስፈር ሂደት ለዘመናት የኖሩበትን የአኗኗር ልምድ እንዲቋረጥ አድርጎታል፤ መተዳደሪያቸውንም ክፉኛ ጎድቶታል። ይህም አልበቃ ብሎ፣ የኦ.ነ.ሠ ደጋፊዎችና አባላት ተብለው የተጠረጠሩት የሁለቱ የጉጂ ዞን ነዋሪዎች ቤቶች ተቃጥለዋል፣ የእርሻ ቦታዎች (የንግድ ስራዎች) ከጥቅም ውጪ ሆነዋል። ይህንንም ያደረጉት የኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይል፣ የኦሮሚያ ፖሊስና የአካባቢው አስተዳደር ሀላፊዎችና የሚሊሻ አባላት ናቸው።

**የእርስ በርስ ግጭት**

በጥር ወር 2011 ዓ.ም. በአማራ ክልል በተደረገ የርስ በርስ ግጭት ቢያንስ 150 ሰዎች ተገድለዋል። የቅማንት የጎሳ አባላት በሚኖሩበት የመተማ አጎራባች፣ ከጥር 2-3፣2011 ዓ.ም. በ24 ሰዓት ውስጥ በተፈጸመ ጥቃት (ምዕራብ ጎንደር ውስጥ ባለ አዋሳኝ ከተማ) ቢያንስ 58 የሚሆኑ ቅማንቶች ተገድለዋል። ጥር 3 ቀን ከተገደሉት መካከል፣ ሶስት ወንድማማቾች፣ ስዩም ታደገ፣ መልካሙ ታደገ እና እያዩ ታደገ እንዲሁም የአጎታቸው ልጅ ሙሉቀን አበበ ይገኙበታል። በአጎራባች ቀበሌ በሚገኙ የቅማንት ነዋሪዎች ላይ የተደረገውን ይህን ጥቃት የፈጸሙት፣ የአካባቢው ሚሊሻና ባለስልጣናት ናቸው። ፋኖ የተባለው የወጣቶች ስብስብም የጥቃቱ ተባባሪ ነበር። ጥቃቱንም የፈጸሙት፣ ጠመንጃ፣ ቦምብ፣ ድንጋይ እና እሳትን በመጠቀም ነበር። ከተማው ውስጥ የነበሩት የኢ.መ.ሀ ወታደሮች ግጭቱን እንዲያስቆሙ ተደጋጋሚ የድረሱልኝ ጥሪ ቢቀርብላቸውም ትዕዛዝ አልተሰጠንም በሚል ሰበብ ምንም እርዳት ሳያደርጉ ቀርተዋል። ይህ የርስ በርስ ግጭት፣ እንደ ጭልጋ፣ ቋራ እና የጎንደር ከተማና በጎንደር ዙሪያ የሚገኙ ከተሞችንም ጎድቷል። በእነዚህ ቦታዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ሲገደሉ፣ በሺዎች የሚቆጠሩት ደግሞ ከየቀያቸው ተፈናቅለዋል። ከጎንደር ከተማ በስተሰሜን በኩል በሚገኝ አዘዞ በሚባል ከተማ፣ ፋኖ የተባለ የወጣት ቡድን፣ መስከረም 18፣ 2012 ዓ.ም ባካሄደው ጥቃት አንድ ህጻንን ጨምሮ አራት የቤተሰብ አባላትን ገድሎ አቃጥሏል። ቡድኑ ይህንን ጥቃት የፈጸመው ቅማንቶች በብዛት በሚኖሩበት በጭልጋ ወረዳ የተገደለን የአንድ አማራ ወጣት ደም ለመመለስ ነበር።

በተከታዮቹ ቀናት፣ ጥቃቱ ወደ ሌላ ቅማንቶች ወደሚኖሩባቸው ስፍራዎች እና ቀጥሎ ደግሞ ወደ ጎንደር ከተማና በአካባቢው ወደሚገኙ ከተሞች ተዛምቷል። ከማዕከላዊ ጎንደር ዞን የፀጥታ ክፍል የተገኘው የመንግስት መረጃ እንደሚያሳየው፣ ከመስከረም አጋማሽ ጀምሮ እስከ ጥቅምት መጀመሪያ 2012 በዘለቀው የርስ በርስ ግጭት፣ ቢያንስ 46 ሰዎች ተገድለዋል። ፋኖ የተሰኘው የወጣት ቡድን ቤት ለቤት እየሄደ የቅማንት ነዋሪዎች ላይ ጥቃት ሲፈጽም፣ የፀጥታ ሀይላት፣ በዋናነት የክልሉ ፖሊስ እና የአካባቢው ሚሊሻ፣ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኞች አልነበሩም።

እነዚህ ጥቃቶችና ያጸፋ-ጥቃቶች፣ በሺዎቸ የሚቆጠሩ አማሮች እና ቅማንቶችን ክልሉ ውስጥ ወዳሉ እንደ ጎንደር፣ ወለቃ፣ ጭልጋ እና አይምባ እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆነዋል። ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ለሚከተሉት የተለያዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተዳርገው ነበር፤ የሰብዓዊ እርዳታን መነፈግ፣ ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ መገደድ እና መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን (የትምህርት፣ የጤና እና መጠለያ) በበቂ ሁኔታ አለማግኘት። በጥር ወር 2011 ዓ.ም. ከቋራ ወረዳ የተሰደደች አንዲት ልጆቿን ብቻዋን የምታሳድግ እናት ፣ ልጆቿ የተራረፈ ምግብ ለማግኘት ሲሉ ትምህርታቸውን አቋርጠው ለሌሎች አርሶ አደሮች የጉልበት ስራ ይሰሩ እንደነበረ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል አስረድታለች።

**የፖለቲካ መካረር**

የፖለቲካው ሁኔታና ያስከተለው የርስ-በርስ ብጥብጥ፣ ነሀሴ 2012 ሊካሄድ ታቅዶ የነበረው ምርጫ በተቃረበበት ሁኔታ እንኳ፣ ተካሮ እንደቀጠለ ነበር። ይሁንና፣ የኢትዮጵያ የብሄራዊ የምርጫ ቦርድ መጋቢት 22 በሰጠው መግለጫ በኮቪድ-19 ምክንያት በገጠመው ችግር የተነሳ ምርጫውን ላልተወሰነ ጊዜ ማስተላለፉን አስታውቋል። የምርጫውን መሰረዝ ያመለከተው ይህ መግልጫ፣ ሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ውጥረት ይበልጥ አባብሶታል። የሚቀጥለው ምርጫ መቼ እንደሚካሄድ አለመታወቁ እና በአሁን ሰዓት ያሉት፣ የክልልና የፌዴራል የህግ አውጪዎችና የስራ አስፈጻሚ አካላት የስልጣን ውክልና መስከረም መጨረሻ 2013 ማብቃቱን ተከትሎ፣ ሊመጣ የሚችለውን ህገ-መንግስታዊ ቀውስ ማስቀረት በሚያስችሉ ስትራቴጂዎች ላይ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል አለመስማማቶች ተካረው ቀጥለዋል።

**ምክረ ሃሳቦች**

ከዚህ በመነሳት፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ለኢትዮጵያ መንግስት፣ የፀጥታ አካላት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መፈጸማቸውን እንዲያቆሙ የሚያስገድድ ልዩ እርምጃ እንዲወስድ ያሳስባል። የኢትዮጵያ መንግስት፣ በፀጥታ ሀይላት ከፍርድ ውጭ የሚፈጸሙ ግድያዎችን፣ የዘፈቀደ እስራቶችን እና ሰዎችን ከቀዬ ማባረርን እንዲያስቆሙ፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም የታጠቁ ቡድኖችን ትደግፋላችሁ የተባሉ ሰዎችን ንብረት ከማውደም እንዲታቀቡ በአስቸኳይ ትዕዛዝ እንዲሰጥ፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ጥሪ ያቀርባል። የኢትዮጵያ መንግስት፣ ንብረትን በማውደም፣ የርስ-በርስ ግጭትን በማባባስ ለተባበሩ፣ የሰብዓዊ መብትን በመጣስ ለተሳተፉ የፀጥታ ሀይላት ምህረት የመስጠትን ባህል ማቆም አለበት። በተጨማሪም፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በፈጸሙ ላይም፣ ነጻ፣ ገለልተኛ፣ የተሟላ እና ተዓማኒነት ያለው ምርመራ እንዲያካሂድ ጥሪ እናቀርባለን። በቂ መረጃ ሲገኝም ፣ የአለም አቀፉ ህግንና ከባድ የሰብዓዊ መብትን በመጣስ የተጠረጠሩ ግለሰቦችን፣ ባለስልጣናት ለፍርድ ሊያቀርቧቸው ይገባል።

# 2. ማጣቃለያ እና ምክረ-ሀሳቦች

## 2.1 ማጠቃለያ

ጥናታችን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ፤ በፀጥታ ሀይሎች፣ ማለትም በኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይል ወታደሮች፣ በኦሮሚያ ፖሊስ እና በየአካባቢው ያሉ የሚሊሻ አባላት አማካኝነት ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንደተፈጸሙ ያሳያል። እነዚህ አካላት የተሰማሩት በኮማንድ ፖስቱ አማካኝነት ሲሆን፣ አላማውም ከኦሮሞ ነጻነት ግምባር ወታደራዊ ክንፍ ተነጥሎ የተቋቋመውን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ለመመከት ነው።

በአማራ የፀጥታ ሀይሎች ዘንድም፣ ተመሳሳይ ግብረ አበርነት እንዳለ ጥናታችን አሳይቷል። ይህ ግብረ-አበርነትም፣ በርስ በርስ ግጭቱ በቀጥታ በመሳተፍ ወይም ደግሞ አንድ ማህበረሰብ ሌላውን ማህበረሰብ ሲያጠቃ አይቶ እንዳላየ በማለፍ ይገለጻል። ፀጥታ የማስጠበቅ ሀላፊነት የነበረበት ሀይል፣ በምዕራብ ጎንደር ውስጥ የተከሰተውን የርስ በርስ ግጭት መከላከል ሳይችል ቀርቷል። በአማራና በቅማንት ህብረተሰብ መካከል የተፈጠረው ግጭት ለወራት ሲቀጣጠል የቆየ ነበር። በጥር ወር 2011 ዓ.ም፣ በመተማ፣ በመስከረም 2012 ዓ.ም ደግሞ በጎንደር ግጭቱ በገሀድ ከመከሰቱ በፊት፣ በአነስተኛ ግጭቶች መልክ ወይንም ቅማንቶች የአማራን አካባቢ ለቀው እንዲወጡ በሚቀሰቅስ ማስታወቂያ አማካኝነት እየታየ ነበር።

በምስራቅ ጉጂ ዞን በሚገኝ ጎሮ ዶላ ወረዳ እና በምዕራብ ጎጂ ዞን በሚገኝ ዱግዳ በተባለ ሌላ ወረዳ፣ 39 ሰዎች ያለፍርድ እንደተገደሉ ጥናቱ ዘግቧል። ከነዚህ መካከል፣ ጥር 2011 እስከ ታህሳስ 2012 ዓ.ም ባሉት ወራት፣ ቢያንስ 25 ሰዎች በፀጥታ ሀይሎች ያለ ፍርድ እንደተገደሉ አምነስቲ ኢንተርናሽናል አረጋግጧል። በአማራ ክልል፣ በፀጥታ ሀይሎች ተባባሪነት ቢያንስ 130 ሰዎች በርስ በርስ ግጭት ህይወታቸውን አጥተዋል።

በአማራ ክልል ውስጥ በሚገኙ በማዕከላዊ ጎንደር እና በምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ በብዙ አጋጣሚዎች ከመስከረም 2011 እስከ ጥቅምት 2012 ድረስ በአማራና በቅማንት ህብረተሰብ መካከል በተከሰቱ በርካታ የርስ በርስ ግጭቶች፣ የፀጥታ ሀይሎች በግብረ-አበርነት ተሳትፈዋል። በተለምዶ ፋኖ እየተባለ የሚጠራው የታጠቀው የአማራ ወጣት ቡድን በቅማንቶች ላይ በሚሰነዝረው ጥቃት ዋነኛው ተዋናይ የነበረ ቢሆንም፣ የክልሉ የፖሊስ ልዩ ሀይል አባላትና የቀበሌ ሚሊሻ አባላት ሚናም ከፍተኛ ነበር።

በኦሮሚያ፣ የኦ.ነ.ሠን እና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ይደግፋሉ ተብለው የሚጠረጠሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በቀበሌ ሚሊሻዎች፣ በኦሮሚያ ፖሊስ እና በኢ.መ.ሀ በዘፈቀደ ታስረዋል። በብዙዎቹ የቀድሞ ታሳሪዎች ላይ ምንም አይነት የወንጀል ክስ ሳይመሰረትባቸው፣ የፀጥታ ሀይሎች፣ እነዚህን እስረኞች፣ ኦ.ነ.ሠን ደግፋችኋል፣ መረጃ አቀብላችኋል፣ ምግብ መግባችኋል በማለት ጠርጥረው እንዳሰሯቸው ነግረዋቸዋል። ተጠርጣሪዎቹም፣ በአማካይ ከአምስት ወራት በላይ በአካባቢው በሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች ምንም ክስ ሳይመሰረትባቸው በእስር እንዲቆዩ ተድርገዋል። በሺዎች የሚቆጠሩት ደግሞ፣ ከመጀመሪያውም ለእስር ቤትነት ባልተሰሩ እንደ ጦላይ የወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ እና ሰንቃሌ ኦሮሚያ ፖሊስ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ባሉ ማቆያ ቦታዎች ተግዘዋል። ታሳሪዎቹ ጠበቆቻቸውን ማነጋገር እንዲችሉ፣ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ፣ ቤተሰቦቻቸውን እንዲያገኙ ወይም ደግሞ ከማሰሪያ ቦታ ውጪ ካለ ሰው ጋር እንዲገናኙ አልተፈቀደላቸውም። የጅምላ እስር በተጀመረበት በጥር ወር 2011 ዓ.ም ቢያንስ 10,000 የሚሆኑ ሰዎች በጦላይ ለእስር ተዳርገዋል።

በፖሊስ ጣቢያዎችና በሳንቃሌ የፖሊስ ማሰልጠኛ ተይዘው የነበሩ እስርኞች ሁኔታ በጣም አስከፊ ነበር። በቂ ምግብ አያገኙም፤ በቂ መኝታ ቦታ አልነበራቸውም፤ ውጭ ወጥተው እንዲናፈሱ አይደረጉም። በሀርቀሎ ፖሊስ ጣቢያ፣ ፖሊስ ህፃናትን ከአዋቂዎች ጋር ቀላቅሎ አንድ አዳራሽ ውስጥ ያጉራቸው ነበር። በኦሮሚያ ኮማንድ ፖስት አማካኝነት ጦላይ ውስጥ ከተለያዩ አካባቢዎች መጥተው አንድ ላይ የተሰባሰቡ እስረኞች ደግሞ የተሀድሶ ስልጠና እንዲወስዱ ይገደዱ ነበር። አሰልጣኞቻቸውም እራሳቸውን እንዲወነጅሉ ያስገድዷቸው ነበር። በእስረኞች ላይ ማሰቃየትና ሌሎች ኢሰብዓዊ አያያዞች ይፈጸሙባቸው ነበር፤ ይህም ወሲባዊ ብዝበዛንና ማሰቃየትን ያካተተ ነበር። ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሁለት ሴቶች ወሲባዊ ጥቃት እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል።

ምስራቅ ጉጂ ዞንና ምእራብ ጉጂ ዞን ውስጥ በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች፣ በኮማንድ ፖስቱ የሚታዘዙ የፀጥታ ሀይሎች፣ ሰዎችን ከየቀያቸው በግድ ማፈናቀልና ንብረታቸውን ማውደምን እንደ ህግ ማስከበሪያ ስትራቴጂ ተጠቅመውበታል።

የኢ.መ.ሀ ወታደሮችና የአካባቢው ባለስልጣናት ሰዎችን ከቀያቸው የማስወጣትን ስራ ከማከናወናቸው አስቀድሞ፣ ነዋሪዎችን አያማክሩም፤ ቅድመ ማስጠንቀቂያም አይሰጡም ነበር።

በርስ በርስ ግጭት የተነሳ ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች፣ አማራዎችም ሆኑ ቅማንቶች፣ በጊዜያዊነት በቆዩባቸው ከተሞች ብዙ ተግዳሮቶች ገጥሟቸዋል፤ እራሳቸውን ለማስተዳደር የሚያስችሏቸው እድሎችም አልነበሯቸውም። ከመንግስት የሚያገኙት እርዳታም አነስተኛ ነበር። ስለሚሰጣቸው በቂ ያልሆና ስረዓት የሌለው ሰብዓዊ እርዳታ ያማርሩ ነበር። ሰዎችን ወደ መኖሪያ ቦታቸው እንዲመለሱ ለማስገደድ ሲባል፣ በመንግስት የሚደረግን እርዳታን የማቋረጥ ሁኔታ ያማርሩ ነበር። ተገደው ቢመለሱ፣ ቀጥሎ ሊከሰት በሚችል የርስ በርስ ግጭት ሰለባ እንሆናለን የሚል ስጋትም ነበረባቸው።

## 2.2 ምክረ- ሀሳቦች

ከእነዚህ ግኝቶች በመነሳት፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በቅርቡ በሚደረገውና በ2010 የተጀመረውን የፖለቲካ ምህዳር መስፋት እና በስደት ላይ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ሀገራቸው መመለሳቸውን ተከትሎ፣ ከፍተኛ ፉክክር እንደሚያስተናግድ ተስፋ በተጣለበት ምርጫ ወቅት፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ጥቃቶች ተባብሰው ይቀጥላሉ የሚል ስጋት አድሮበታል። በተለያዩ ፖለቲካዊና ማህበረሰባዊ ክፍሎች መካከል በሚደረጉ ፉክክሮች ውስጥ፣ የፀጥታ ሀይሎች ወገንተኝነት ማሳየትን እንዲያቆሙና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መፈፀማቸውን እንዳይቀጥሉ፣ መንግስት ልዩ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

በመሆኑም፣ መጭው አጠቃላይ ምርጫ ከመካሄዱ በፊት፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በአስቸኳይ ሊፈጸሙ ይገባቸዋል የሚላቸውን ምክረ- ሀሳቦች ለኢትዮጵያ መንግስት እንደሚከተለው ለይቶ ያቀርባል፤

## 2.2.1 ለኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር

- በምስራቅና በምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ህግን ለማስከበር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ የፀጥታ ሀይሎች  የሚፈፅሙትን ያለ ፍርድ መግደልን፣ በጅምላ ማሰርን፣ አስገድዶ ማፈናቀልን እና ንብረት ማውደምን እንዲያቆሙ ይፋዊ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፉ፤
- በአለም-አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ህጎችና ደንቦች በተደነገገወ መሰረት፣ የፀጥታ ሀይሎች፣ በትጥቅ የተደገፉ ግጭቶችንና  የርስ በርስ ብጥብጦችን ጨምሮ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ የፀጥታ ስጋቶችን ለመቆጣጠር በሚሰማሩበት ጊዜ ፣ ሊከተሏቸው ስለሚገቡ አለም-አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ህጎችና ደንቦች፣ የሚኖራቸውን የስልጣን ገደብና የሚገዙባቸውን ድንጋጌዎች ለህዝብ ተደራሽ በሆነ መንገድ በፅሑፍ ይፋ እንዲያደርጉና እንዲያብራሩ፤
- የኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይል፣ ህግን ለማስከበር  የሚደረገውን የዘመቻ ስራ ጨምሮ ፣ የፀጥታውን ዘርፍ የሚቆጣጠር ውጤታማ፣ ተዓማኒ፣ ከሲቪሉ ማህበረ-ሰብ የተውጣጣ እና ነጻ አካል በአስቸኳይ እንዲያቋቁሙ፤
- በዘፈቀደ ወይም በጅምላ ያለፍርድ የሚፈጸሙ ግድያዎች ልዩ ዘጋቢን ጨምሮ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰባዓዊ መብቶች አያያዝ ልዩ ግብረ-ሀይል ሀገሪቱን እንዲጎበኙ እንዲጋብዙ፤

## 2.2.2  ለመከላከያ ሚኒስቴር

- በርስ በርስ ግጭት በቀጥታ የተሳተፉ የፀጥታ ሀይል አካላትን ከሰራዊቱ  እንዲገለሉ እንዲያደርግ እና ለፈጸሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነፃ፣ ገለልተኛ፣ የተሟላ፣ ውጤታማና ተዓማኒ ምርምራ እንዲያደርግ፤ በቂ መረጃ ሲገኝም፣ በአለም ዓቀፍ ህግ የተቀመጠውን የሰብዓዊ መብት ጥሰትን በመፈጸም ምክንያታዊ በሆነ ደረጃ የተጠረጠሩትን ለፍርድ እንዲቀርቡ እንዲያደርግ።

## 2.2.3 ለሰላም ሚኒስቴር፣ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን  እና ለጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ

- በህገ-ወጥ ግድያ፣ የአካል ጉዳት በማድረስ እና ሰዎችን ከቀያቸው በማፈናቀል የተሳተፉ የቡድኖች መሪዎችና አባሎቻቸው ላይ ምርማራ እንዲያደርጉና ለህግ እንዲያቀርቡ፤
- በኮማንድ ፖስቱ ትዕዛዝ፣ በምስራቅና በምዕራብ ጉጂ ዞኖች በተሰማሩበት ወቅት በአስገድዶ መድፈርና በወሲባዊ ጥቃት የተከሰሱ  የፀጥታ ሀይሎች ላይ ነጻ፣ ገለልተኛ፣ የተሟላና ተዓማኒ ምርምራ እንዲያደርጉ፤
- በኦ.ነ.ሠ በተፈጸሙ ግድያዎችና አፈናዎች፣ በተለይ በኦሮሚያ ክልል፣ ነጻ፣ ገለልተኛ፣ የተሟላና ተዓማኒ ምርምራ እንዲያደርጉ፤
- በጥር ወር 2011 ዓ.ም በመተማና ቋራ እንዲሁም በጠገዴ ወረዳዎች፣ በመስከረምና በጥቅምት ወራት 2012 ዓ.ም ደግሞ በአዘዞ፣ በጎንደር፣ ወለቅ/ አርጎባና ጭልጋ የተፈጸሙትን የርስ በርስ ግጭቶች በማነሳሳት፣ በማስተባበር እና በማስፈጸም የተጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ ምርመራ እንዲያደርጉ እና ለህግ እንዲያቀርቡ፤
- የኢ.መ.ሀ አባላትን፣ የክልል ፖሊስ ልዩ ሀይልን እና ሰብዓዊ መብትን ለማስከበር የተሰማሩትን የቀበሌ ሚሊሻዎችን ጨምሮ፣ ለሁሉም የፀጥታ ሀይሎች ውጤታማ ስልጠና እንዲሰጡ፤
- ያለፍርድ ግድያዎችን፣ አስገድዶ መድፈርን እና ሌሎች ኢሰብዓዊ አያያዞችን ጨምሮ በማንኛውም ህገወጥ ግድያዎች ላይ የተሳተፉ ሰዎች ላይ መንግስት እያደረገ ስላለው የምርመራና የፍርድ ሂደት በተከታታይ በጽሑፍ  እንዲያሳውቁ፤
- ተፈናቃዮች  ወደመኖሪያ ቀያቸው እንዲመልሱ ፍቃድ እንዲሰጡና ሂደቱንም እንዲያሳልጡ፤
- በእስር ባሉ ሰዎች ላይ  የሚፈጸሙ ማንኛውም አይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣  የአስገድዶ መድፈር እና ወሲባዊ ጥቃቶች  ላይ ምርመራ እንዲያደርጉና ወንጀለኞችንም  ለህግ እንዲያቀርቡ፤
- በአማራና በቅማንት ህዝብ መካከል በተፈጠረው የርስ በርስ ግጭት የፀጥታ ሀይል አባላት (የኢ.መ.ሀ፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የአማራ ክልላዊ ፖሊስ እና የየአካባቢ አስተዳደርና ሚሊሻ) ሚና ምን ይመስል እንደነበር ነጻ፣ ገለልተኛ፣ የተሟላ እና ተዓማኒ ምርመራ እንዲያደርጉ፤

## 2.2.4  ለሰላም ሚኒስቴር

- በርስ በርስ ግጭትና በፀጥታ ሀይሎች አማካኝነት ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች፣ የምግብ፣ ምግብ ነክ ያልሆኑ፣ የከለላ፣ የንፅህናና የጤና አገልግሎት አቅርቦትን ጨምሮ፣ የሰባዓዊ እርዳታ አገልግሎት እንዲያቀርቡና አቅርቦቱንም እንዲያሳልጡ፤
- የንብረት ውድመትና ቃጠሎ ለደረሰባቸው፣ መተዳደሪያቸውን፣ እርሻቸውንና የቀንድ ከብቶቻቸውን ላጡ ሰዎች በአስቸኳይ ተገቢውን ካሳ እንዲሰጡ፤
- በአማራ ክልል ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች፣ ተጠባቂና በቂ የሰብዓዊ እርዳታ እንዲያቀርቡና አቅርቦቱንም እንዲያሳልጡ፤
- ወንጀልን ለመቆጣጠር፣ አካታች፣ ግልጽ፣ ፍትሀዊነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በአሁኑ ሰዓት ያሉትን የፍትህ እርምጃዎች መገምገም፤ ይህንንም ለማድረግ፣ ከባድ የሰብዓዊ መብት ጥስቶች ለሚፈጸምባቸው ሰለባዎች የሚሰጥ የማካካሻና የፈውስ መብትን እና የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ከባድ ጥሰቶች ህግን ያማከሉ የተባበሩት መንግስታት መሰረታዊ መርሆችና መመሪያዎችን እንዲከተሉ፤
- ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች በፈቃደኝነትና፣ ያለስጋት በክብር ወደ ቦታቸው መመለሳቸውን እንዲያረጋግጡ፣

- በሀገሪቱ ውስጥ እየተከሰቱ ያሉ የርስ በርስ ግጭቶችን ለማቃለል፣ የችግሮቹን መሰረታዊ ምንጮች በመለየት፣ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂዎችን እንዲነድፉና እንዲተገብሩ፤

## 2.2.5 ለተባበሩት መንግስታት፣ ለአፍሪካ ሕብረት እና ለኢጋድ

- የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱትን ምክረ-ሀሳቦች፣ በተለይም ምርጫን አስመልክቶ የተሰጡትን አፋጣኝ ሀሳቦች ቅድሚያ ሰጥቶ ከነሀሴ 2012 ምርጫ በፊት እንዲተገብር እንዲያበረታቱ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ምርመራ እንዲያደርጉና ሪፖርት እንዲያቀርቡ ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ፣ለሀገር-በቀል ሰብዓዊ መብት ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት ድጋፍ እንዲሰጡ፤
- የምርጫውን ዕለት ጨምሮ፣ በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫ ወቅት ወይም ምርጫው ካበቃ በኋላ ስለሚደረጉ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሁኔታዎች፣ የሚመለከታቸው የሰብዓዊ መብት አካላት ቁጥጥርና ግምገማ ያደርጉ ዘንድ ማበረታቻ እንዲሰጡ፤
- ዘላቂነት ላላቸው፣ ግጭትን በመተንበይ፣ በመከላከልና መፍትሄ በመስጠት ለሚያግዙ ስትራቴጂዎች ድጋፍ እንዲሰጡ፣
- የቫን ቦቨን/ ባስዩኒ መርሆች እና የአፍሪካ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን መሰረት በማድረግ፣ ባለፉት ጊዜያት የተወረሱ የጭካኔ ድርጊቶችን ለማስወገድ፣ አካታች፣ ግልጽና ሚዛናዊ የፍርድ ሂድቶችን እንዲያበረታቱና ድጋፍ እንዲሰጡ።

## 2.2.6 ለአውሮፓ ሕብረት፣ ለአሜሪካ መንግስት፣ ለታላቋ ብሪታኒያ፣ ለካናዳ፣ ለቻይና፣ ለኬንያ፣ ለደቡብ አፍሪካ

- የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱትን ምክረ-ሀሳቦች፣ በተለይም ምርጫን አስመልክቶ የተሰጡትን አፋጣኝ ምክረ-ሀሳቦች ቅድሚያ ሰጥቶ ከነሀሴ 2012 ምርጫ በፊት እንዲተገብር እንዲያበረታቱ፤
- የሲቪል ፖሊስ ስልጠናን ለመስጠት የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሰጡ፣
- በሀገሪቱ ውስጥ ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች አፋጣኝ ሰብዓዊ እርዳታ መስጠት የሚያስችል የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያቀርቡ፤
- ዘላቂነት ላላቸው፣ ግጭትን በመተንበይ፣ በመከላከልና መፍትሄ በመስጠት ለሚያግዙ ስትራቴጂዎች ድጋፍ እንዲሰጡ፤
- የቫን ቦቨን/ ባስዩኒ መርሆች እና የአፍሪካ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን መሰረት በማድረግ፣ ባለፉት ጊዜያት የተወረሱ የጭካኔ ድርጊቶችን ለማስወገድ፣ አካታች፣ ግልጽና ሚዛናዊ የፍርድ ሂደቶችን እንዲያበረታቱና ድጋፍ እንዲሰጡ፤
- የፀጥታ ሀይሎች የሰብዓዊ መብቶችን ያከብሩ፣ ይጠብቁና ከፍ ከፍ ያደርጉ ዘንድ አስቸኳይ ያቅም ግንባታ እርዳታ እንዲሰጡና የማሳለጥ ስራ እንዲሰሩ፤
- የአካባቢ ሲቪክ ማህበራት፣ የዜና ማሰራጫዎችና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች የመቆጣጠር፣ የመሰነድ፣ የተሟጋችነትና የዘመቻ ስራ በመስራት የሰብዓዊ መብቶችን ይከላከሉና ከፍ ከፍ ያደርጉ ዘንድ የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያሳልጡ።

# ህግ ከማስከበር በዘለለ

## በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በኢትዮጵያ የፀጥታ ሀይሎች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

አሁን በስልጣን ላይ ባለው መንግስት በ2010 ዓ.ም  የተጀመረው ፖለቲካዊ ለውጥ ሀገሪቱን ተጠናውተዋት ከነበሩት አስከፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ ከፍርድ ውጭ ሰው ከመግደል፣ ሰዎችን ከማሰቃየትና መሰል ሌሎች ኢሰብዓዊ አያያዞች፣ ስዎችን  ያለፈቃዳቸው  እንዲሰወሩ ከማድረግ እና ከመሳሰሉ የመብት ጥሰቶች እንድትላቀቅ አጋጣሚውን ፈጥሮላታል።  የሰብዓዊ መብት ሁኔታዎችን ለማሻሻል የተወሰዱ የመጀመርያ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በፀጥታ ሀይላት ያለማሳለስ እየተወሰዱ ያሉ ኋላቀር የሀይል እርምጃዎች በዘላቂነት ሊቀጥል የሚገባውን ለውጥ ባጭር እንዳያስቀሩት ያሰጋል።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ በ2011 በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በተከስቱ የርስ በርስ ግጭቶች ላይ ጥናት አካሂዶ፣ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይል፣ የክልል ልዩ የፖሊስ ሀይል፣ ያካባቢው ያስተዳደር ሀላፊዎች፣ ከታጠቁ ሀይሎችና ከወጣት ቡድኖች ጋር በማበር፣ በአንዳንድ የአማራና የኦሮሚያ ክፍሎች፣ ከባድ/ከፍተኛ የሰባዓዊ መብት ጥሰቶች እንደፈፀሙ አረጋግጧል።